OSSE

# የማህበረሰብ አገልግሎት የምረቃ መስፈርት፥ የ 2022-23 የትምህርት ዓመት

## መመሪያ ለተማሪዎች እና ቤተሰቦች

## በ 2023 ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናቀቅ አለብኝ?

አዎ። በ 2023 ከዲሲ የሕዝብ እና የሕዝብ ቻርተር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመረቅ፣ ተማሪዎች የ**12** ሰዓታት የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናቀቅ አለባቸው። ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ተመዝግበው እያሉ የማህበረሰብ አገልግሎት ሰዓታት መጠናቀቅ አለባቸው። አንድ ተማሪ **9**ኛ ክፍል ከመግባቱ/ቷ በፊት የሚደረግ የማህበረሰብ አገልግሎት የምረቃው መስፈርት ውስጥ አይቆጠርም። ተማሪዎች የተጠናቀቁ ሰዓቶችን እንዴት ማስገባት እንዳለባቸው ትምህርት ቤቶች ማስተማር አለባቸው።

## እንደ ማህበረሰብ አገልግሎት ለመቆጠር ምን ብቁ ይሆናል?

የማህበረሰብ አገልግሎት ማለት ለህብረተሰብ/ለማህበረሰብዎ ጥቅም ሲባል የሚጠናቀቅ ክፍያ የማይደረግበት ተግባር ማለት ነው። ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤትዎ በተደራጁ ተግባራት አማካኝነት፣ ማለትም ለትርፍ ባልተቋቋመ ወይም ለትርፍ በሚሰራ ድርጅት ወይም በቨርቹዋል መቼት (እንደ የመስመር ላይ ትምህርት) አማካኝነት የተጠናቀቁ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ማጽደቅ አለባቸው።

| የማህበረሰብ አገልግሎት ምሳሌዎች | ያልተፈቀዱ |
|---|---|
| • በህብረተሰብ የሚጣል ቆሻሻን ማጽዳት<br>• እንደ ተማሪ ተወካይ የሕዝብ አካል ወይም ኮሚቴ ላይ የሚደረግ አገልግሎት<br>• የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ዓይነት አካል የሆነ አገልግሎት<br>• ለፖለቲካ ምርጫ ቅስቀሳ በጎ ፈቃደኛ መሆን | • ለተማሪዎች ደመወዝ የሚከፈልባቸው ተግባራት፣ እንደ የላቀ የኢንተርንሺፕ ፕሮግራም፣ የ በጋ የወጣት ቅጥር ፕሮ ግራም ወይም የውጭ ቅጥር ዓይነት<br>• የተማሪው/ዋን ወይም የተማሪው/ዋን ቤተሰብ መጥቀም ብቻ ላይ ያተኮሩ ተግባራት፣ ለምሳሌ ወንድም ወይም እህት ህጻንን መጠበቅ |

## ገና አሁን ወደ ዲሲ የተዛወርኩ ከሆነስ?

የትምህርት ዓመቱ ከጀመረ በኋላ ከሌላ ክልል ወደ ዲሲ የህዝብ ወይም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት የተዛወሩ በሁለተኛ ደረጃ ነባር የሆኑ ተማሪዎች ለ2023 የምረቃ መስፈርቶች የማህበረሰብ አገልግሎትን ማጠናቀቅ አይጠበቅባቸውም።

## ጥያቄዎች?

ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን በትምህርት ቤትዎ ውስጥ አስተዳዳሪን ወይም የመመሪያ አማካሪን ያነጋግሩ።